ፍኖተ
# ነፃነት
ፍኖተ ነፃነት መጋቢት 29 ቀን 2005 ዓ.ም.
የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!
ሁለተኛ ዓመት ቅጽ 2 ቁ. 71

## “ህወሓት የአማራ ፖለቲከኞች ከኢትዮጵያዊ ብሔረተኝነት ርዕዮተአለም እንዲወጡ ማድረግ ይፈልጋል”



አቶ ጃዋር መሀመድ የፖለቲካ ተንታኝ

6

## ዘረኝነት በቂሊንጦ እስር ቤት 4

## በቤንች ማጂ አማርኛ ተናጋሪዎችን ማፈናቀል ዳግም ተጀመረ 9

## ‹‹የሃይማኖት ነጻነት በኢትዮጵያ አልተከበረም››

ጠበቃ ተማም አባቡልጉ 10

## ምርጫ እስኪያልፍ ሙዚቃ ቤቶች የቴዲ አፍሮና የፀጋዬ እሸቱን ዘፈኖች መክፈት ተከለከሉ 9

## የታፈኑት የአንድነት አመራር የታሰሩበትን ምክንያት የሚገልፅ ማስረጃ ተከለከሉ 9

ፍኖተነፃነትጋዜጣሐምሌ2003ዓ.ምተመሰረተ።

ፍኖተ ነፃነት በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ስር የሚታተም በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ጋዜጣ ነዉ።

ጋዜጣችን ሚዛናዊና ነፃ ጋዜጣ ሆኖ ማገልገል መርሁ ነው። ማንኛውም ሀሳብና አመለካከት የሚስተናገድበትና የሚንሸራሸርበት እንዲሆን እንሻለን። ሰፊ የሚዲያ ሽፋን ያለው ኢህአዴግም በዚህ ሚዲያ አቋሙንና ፖሊሲውን ለማግለፅ ቢፈልግ መድረኩ ክፍት ነው።

## ርእሰ አንቀጽ

# መንግስት የህሊና እስረኞች ላይ የሚያደርሰውን የግፍ አያያዝ ሊያቆም ይገባል!

በህሊና እስረኞች ቁጥር ከፍ በማለቱ፣ ሀገሪቱ ውስጥ ባሉ የተለያዩ ወህኒ ቤቶችን አጣበዋል፡፡ በፖለቲካ አመለካከታቸው፣የመብት ጥያቄ በማንሳታቸው፣ የሃይማኖት ነፃነት ጥያቄ በማቅረባቸውን በሌሎችም ምክንያቶች ወንጀል ሳይፈፅሙ የሚታሰሩት የህሊና እስረኞች በግፍ መታሰራቸው ሳያንስ፣ በወህኒቤት ውስጥ ሆነው የተለያዩ የግፍ ድርጊቶች ይፈፀምባቸዋል።

የኢህአዴግ መንግስት በውጫዊና በውስጣዊ ምክንያቶች በተናወጠ ቁጥር በእስረኞች ላይ በተለይም በህሊና እስረኞች ላይ የግፍ በትር የመምዘዝ እኩይ ልምድ አለው። ለማሳያነት ያክልም በምርጫ 97 ማግስት እና የቀድሞው ጠቅላይ ሚንስትር አቶ መለስ ዜናዊ ሞት ይፋ ሲደረግ ስቃችኋል፣ ደስብሏችኋል በሚል የተደበደቡ፣ ከሚኖሩበት ስፍራ የተዛወሩ፣ዛቻና ማስፈራሪያ ደረሰባቸው ዜጎች መጥቀስ ይቻላል።

በኢትዮጵያ ወህኒ ቤቶች ውስጥ የሚፈፀሙ ሆኖም በሚዲያ ለመዘርዘር የመይመቹ በርካታ ሰብአዊነት የጎደላቸው የግፍ ድርጊቶች እንዳሉ የሚያመላክቱ መረጃዎች በየጊዜው ለጋዜጣችን ይደርሳሉ። የእነዚህን መረጃዎች እውነትነት ለማረጋገጥ የኢትዮጵያ መንግስትን የእስረኞች አያያዝ የያሳዩ አለም አቀፍ ሪፖርቶችን መመልከት በቂ ነው።

በህግ ጥበቃስር የሚገኙ እስረኞች በህገመንግስት የተረጋገጡ መብቶች አሏቸው። ከዚህ ውስጥ የሚጠቀሰው እስረኞች በወዳጅ ዘመዶቻቸውና ቤተሰቦቻቸውና በሃማኖት አባቶቻቸው መጎብኘት መብት ነው። ሆኖም አብዛኞቹ የህሊና እስረኞች ከቅርብ ቤተሰቦቻተው ውጪ በሌሎች እንዳይጠየቁ ክልከላ ደርሶባቸዋል።
ከዚህ በተጨማሪ በወህኒ ቤቱ ውስጥ ህገ ወጥ ክትትልና ሌሎች በደሎችም ይደርስባቸዋል።
በድፍረት መናገር እንደሚቻለው የኢትዮጵያ ወህኒ ቤቶች መንግስት ተቀናቃኞቼ ናቸው የሚላቸውን ዜጎች የሚበቀልበት ስፍራ እንጂ ማረሚያ ቤቶች አይደሉም።

ለመብቱ መከበር የታገለ ዜጋ ያለጥፋቱ የሚታሰርበትና በእስር ላይ ሆኖ ጥቃትን ሚቀበልበት ስፍራ እንደምን ማረሚያ ቤት ልንለው እንችላለን?

የህሊና እስረኞቹ በግፍ መታሰራቸው ሳይበቃ በመንግስት በሚላኩ "ሽማግሌ ነን" ባዮች ባልሰሩት ወንጀል ይቅርታ እንዲጠይቁ የተለያየ ጫና ይደረግባቸዋል፡፡ ሆኖም በደል ሲደርስባቸው "ሽማግሌ ነን" ባዮቹ ጆሮ ዳባልበስ ማለታቸው አስተዛዛቢ ነው።

ለህሊና እስረኞች በተቃዋሚ ፓርቲዎችም ተገቢውን ትኩረት አግኝተዋል ብሎ ለመናገር አስቸጋሪ ይመስለናል። በርግጥ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ የህሊና እስረኞችን ለማሰብ በየወሩ የሻማ ማብራት መርሀግብር ያዘጋጃል፤ ይህ በሁሉም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሊተገበር የሚገባው መልካም ተሞክሮ ነው። ሆኖም ተቃዋሚዎች ከዚህ ባለፈ መንግስት የኢህአዴግ ባለስልጣናት በአምባገነንነት እብሪት በህሊና እስረኞች ላይ የሚፈፅሟቸውን ኢሰብአዊ በደሎች እንዲያቆሙ የሚያስችል ጠንካራ የተቃውሞ እንቅስቃሴ በማድረግ አስፈላጊውን መስዋዕትነት ለመክፈል መቁረጥ ይገባቸዋል።

የኢትዮጵያ ህዝብም በአመለካካታቸው ብቻ የታሰሩ ዜጎችን ጉዳይ በቅርብ መገታተል ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር በመሆን መንግስት የሚያደርሰውንም ግፍ ለመቃወም መነሳት ይጠበቅበታል።

ከሁሉ በላይ ለመንግስት ሊገባው የሚገባው ቁም ነገር ግን ታጋዮችን በማሰር ብሎምም በመግደል የሚቆም የነፃነት ትግል እንደሌለ ነው። አዎ! ኢህአዴግ ሆይ ብዙዎች የታሰሩለት፣ ብዙዎች የተሰቃዩለትና የሞቱለት ነፃነት ፈጠነም ዘገየ እንደሚመጣ ቅንጣት አንጠራጠርም።

ጋዜጣችንን "ፍኖተ ነፃነት" ብለናታል "ፍኖት" ማለት መንገድ ማለት ሲሆን ከነፃነት ጋር ሲጣመር የነፃነት መንገድ ማለት ነው::

# አንዱዓለም አራጌ እና ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ሰኞ በዳግም ቀጠሮ ፍርድ ቤት ይቀርባሉ

የአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ አመራር አቶ አንዱዓለም አራጌ፣ አቶ ናትናኤል መኮንን እና እውቁ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ፣ አቶ አንዱዓለም አያሌው፣ አቶ ዮሐንስ ተረፈ፣ ሻምበል የሺዋስ ይሁንዓለም፣ አቶ ክንፈሚካኤል ደበበ እና አቶ ምትኩ ዳምጤን ጨምሮ 24 ሰዎች በተከሰሱበት ክስ ከላይ ስማቸው የተጠቀሱ 8ቱ የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ ወንጀል ችሎት የወሰነውን የጥፋተኝነት ውሳኔ በመቃወም ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢጠይቁም እስካሁን ውሳኔ ሳይሰጥ ለ 4 ጊዜ ተቀጥሮ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ሰኞ መጋቢት 30 ቀን 2005ዓ.ም. 6 ኪሎ በሚገኘው የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተቀጠረው መሰረት ከጠዋቱ 3ሰዓት ውሳኔ እንደሚሰጥ ይጠበቃል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከላይ በተጠቀሰው ክስ ተፈርዶበት አቃቂ ቃሊቲ በሚገኘው ቂሊንጦ ወህኒ ቤት በልዩ ጥበቃ ያለው አቶ ናትናኤል መኮንን የጥበቃ ኃላፊዎች ለአንድ ወር ከቤተሰብ እንዳይገናኝ የወሰኑበትን ቅጣት በመቃወም ለአንድ ሳምንት ምግብ ሳይበላ የርሃብ አድማ ማድረጉን ተከትሎ በእስር ቤት ያሉ ጓደኞቹና ከተከላካይ ጠበቆቹ አቶ አበበ ጉታ እና አቶ ደርበው ተመስገን ጋር ባደረጉት ውይይት አሁን ምግብ መብላት መጀመሩን ጠበቃው አቶ አበበ ጉታ በተለይ ለፍኖተ ነፃነት ገልፀዋል፡፡

አቶ አበበ ጉታ አያይዘውም "አቶ ናትናኤልን ካነጋገርን በኂላ ከጥበቃ ክፍል ኃላፊ ከሆኑት ሐጎስ ጋር በጉዳዩ ዙሪያ ብንነጋገርም በቀጥታ የሚመለከተው ኃላፊ ልናገኛቸው ባለመቻላችን የተጣለበት ቅጣት አግባብ እንዳልሆነ እና ቅጣቱም በአስቸኳይ እንዲነሳ በወቅቱ ላገኘናቸው መልዕክት አስተላልፈናል፤ እነሱም ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ መልዕክቱን እንደሚያደርሱ አረጋግጠውልናል" ሲሉ ገልፀውልናል፡
:

የአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ አመራር አቶ አንዱዓለም አራጌ፣ አቶ ናትናኤል መኮንን እና እውቁ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ፣ አቶ አንዱዓለም አያሌው፣ አቶ ዮሐንስ ተረፈ፣ ሻምበል የሺዋስ ይሁንዓለም፣ አቶ ክንፈሚካኤል ደበበ እና አቶ ምትኩ ዳምጤን ጨምሮ 24 ሰዎች በተከሰሱበት ክስ ከላይ ስማቸው የተጠቀሱ 8ቱ የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ ወንጀል ችሎት የወሰነውን የጥፋተኝነት ውሳኔ በመቃወም ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢጠይቁም እስካሁን ውሳኔ ሳይሰጥ ለ 4 ጊዜ ተቀጥሮ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ሰኞ መጋቢት 30 ቀን 2005ዓ.ም. 6 ኪሎ በሚገኘው የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተቀጠረው መሰረት ከጠዋቱ 3ሰዓት ውሳኔ እንደሚሰጥ ይጠበቃል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከላይ በተጠቀሰው ክስ ተፈርዶበት አቃቂ ቃሊቲ በሚገኘው ቂሊንጦ ወህኒ ቤት በልዩ ጥበቃ ያለው አቶ ናትናኤል መኮንን የጥበቃ ኃላፊዎች ለአንድ ወር ከቤተሰብ እንዳይገናኝ የወሰኑበትን ቅጣት በመቃወም ለአንድ ሳምንት ምግብ ሳይበላ የርሃብ አድማ ማድረጉን ተከትሎ በእስር ቤት ያሉ ጓደኞቹና ከተከላካይ ጠበቆቹ አቶ አበበ ጉታ እና አቶ ደርበው ተመስገን ጋር ባደረጉት ውይይት አሁን ምግብ መብላት መጀመሩን ጠበቃው አቶ አበበ ጉታ በተለይ ለፍኖተ ነፃነት ገልፀዋል፡፡

አቶ አበበ ጉታ አያይዘውም "አቶ ናትናኤልን ካነጋገርን በኂላ ከጥበቃ ክፍል ኃላፊ ከሆኑት ሐጎስ ጋር በጉዳዩ ዙሪያ ብንነጋገርም በቀጥታ የሚመለከተው ኃላፊ ልናገኛቸው ባለመቻላችን የተጣለበት ቅጣት አግባብ እንዳልሆነ እና ቅጣቱም በአስቸኳይ እንዲነሳ በወቅቱ ላገኘናቸው መልዕክት አስተላልፈናል፤ እነሱም ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ መልዕክቱን እንደሚያደርሱ አረጋግጠውልናል" ሲሉ ገልፀውልናል፡፡

**በውጭ ሀገር ለምትገኙ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ቀደም ሲል ለፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ የህትመት መሳሪያ ማደራጃ ለመግዛት እንዲቻል ጥሪ መቅረቡ ይታወሳል፡፡ በጥሪው መሰረት በርካታ ወገኖቻችን ተግባራዊ ምላሽ እየሰጡ መሆናቸው በወገኖቻችን እንድንኮራ አድርጎናል፡፡ ይሁን እንጂ በርካታ ወገኖቻችን በገንዘብ አላላኩ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ በመጠየቃቸው ይህን ማብራሪያ አቅርበናል፡፡ ገንዘቡ የሚገባው በቀጥታ በፍኖተ ነጻነት አካውንት ነው፡፡**

1/በኦንላይን እርዳታ ለማድረግ ለምትፈልጉ በፔይፓል (pay pal secure payment)
እነዚህን ድህረ ገጾች ይጎብኙ

http://www.fnotenetsanet.com/
http://www.andinet.org/
http://www.andinetusa.org/

2/ በኤሌክትሮኒክስ ቀጥታ ለምታስተላልፉ

Andinet North America (Finote Netsanet News Paper)
Bank Name : Wells Fargo
ACC# 753-085-0978
Routing # 054-001-220

3/ በቼክ ወይም በገንዘብ ማዘዣ (money order)

Andenet North America (Finote Netsanet News Paper)
P.O.Box 48355
Washington DC 20002
Tel. (202) 462-0556 Fax: (202) 462-0557

ማሳሰቢያ ፡ ገንዘቡን ገቢ ካደረጋችሁ በሁዋላ በሚቀጥለው ኢሜይል አድራሻ ብታሳውቁን ለስራችን ጥራት ይረዳናል፡፡
Email: info@andinetusa.org
ስለትብብራችሁ አስቀድመን ከፍተኛ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡
በመላው አለም የምትገኙ ወገኖቻችንም ይህን መረጃ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ፡፡

የፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ ዝግጅት አስተባባሪ ኮሚቴ በሰሜን አሜሪካ

# ዘረኝነት በቂሊንጦ እስር ቤት

እንደሚታወቀው ከህወሐት/ኢህአዴግ ሥርዓት መገለጫ ባህሪያት አንዱና ዋነኛው ዘረኝነት ነው፡፡ ይህ ዘረኛ ሥርዓት ዓላማውን ለማሳካት ሲል በሀገሪቱ ባሉ ተቋማት በሙሉ ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን በህወሐት ካድሬዎች እንዲያዙ ያደርጋል፡፡
በብዙ ተቋማት ደግሞ ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን ብቻ ሳይሆን ከላይ እስከታች ያለውን ቦታ በእነዚህ የአንድ ብሔር ድርጅት ካድሬዎች ተይዞ ይገኛል፡፡ የፌዴራል ተቋም ሆኖ ሳለ የሚመስለው ግን የአንድ ክልል ተቋም ነው፡፡ ከእነዚህ ተቋማት ውስጥ በፌዴራል ማረሚያ ቤት ሥር ያሉት የቃሊቲ፣ ቂሊንጦ፣ ዝዋይ፣ ሸዋ ሮቢትና የድሬደዋ እስር ቤቶች ይገኙበታል፡፡ በእነዚህ እስር ቤቶች የሚፈፀመው ዘረኝነት ተመሳሳይነት ቢኖረውም በቃሊቲና ቂሊንጦ እስር ቤቶች የሚፈፀመው ግን እጅግ የከፋ ነው፡፡
በሌሎች ያለውን ለጊዜው እንተወውና ለዛሬ በቂሊንጦ እየተፈፀመ ያለውን ላውጋችሁ፡፡ በቂሊንጦ ከባድ ጥበቃ ማ/ቤት የመምሪያ ኃላፊዎች፣ የክፍል ኃላፊዎች፣ የሦስቱም ዞኖች ኃላፊዎች ሙሉ በሙሉ የህወሐት ካድሬዎች ሲሆኑ ጥበቃዎች፣ ቤተሰብ አገናኞችና ሌሎችም የሥራ ቦታዎች ከሞላ ጎደል በእነርሱ የተያዙ ናቸው፡፡ ይህ የቂሊንጦ እስር ቤት በ3 ዞኖች የተከፈለ ነው፡፡
በእነዚህ ዞኖች እየተፈፀመ ያለው የዘረኝነት ተግባር ተመሳሳይ ቢሆንም በዞን ሁለት እየተፈፀመ ያለው ግን ከሁሉ የከፋ ነው፡፡

በዚህ ዞን ከ15 ዓመት እስከ ሞት ድረስ ያሉ ፍርደኞች የሚታሰሩበት ቦታ ነው፡፡
በዚህ ዞን ብዙ የፖለቲካ እስረኞች ይገኛሉ፡፡ በግንቦት 7፣ በኦነግ፣ በኦብነግ፣ በአርበኞችና በሌሎች የተከሰሱ እስረኞች ይገኙበታል፡፡ ከእነዚህ የፖለቲካ እስረኞች ጋር ሰላምታ የተለዋወጠ፣ያወራ፣አብሮ የሄደና ማንኛውንም ማህበራዊ ግንኙነት የፈጠረ እስረኛ ቢሮ እየተጠራ ዛቻ ፣ማስፈራራትና ድብደባ ይፈፀምበታል፡፡ በተለይ በግንቦት 7 እና በኦነግ ከተከሰሱ እስረኞች ጋር የሚቀራረቡ የአማራና የኦሮሞ ተወላጆች ቁም ስቃያቸውን ነው የሚያዩት፡፡ በዞኑ ብዛት ያላቸው ወሬ አቀባዮች ወይም በእስር ቤት ቋንቋ አስጠጪዎች ያሉበት ቦታ ነው፡፡
እነዚህ ደግሞ የእነርሱ ብሄር አባላት ናቸው፡፡ እነዚህ ከሌላው በተለየ መልኩ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞችን እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ክበቡን፣ህብረት ሱቁን እንዲይዙ ይደረጋል፡፡ በእስር ቤቱ ያልተፈቀዱ ነገሮች (ሲጋራ፣ ጫት፣ አደንዛዥ ዕፅ ወዘተ…) እንዲያስገቡና እንዲሸጡ ይመቻችላቸዋል፡፡ የሚያገኙትንም ጥቅም ከኃላፊዎች ጋር ይጋራሉ፡፡
በነፃነት የፈለጉበት ቦታ ሄደው የመምጣት፣ ከተማ ሄደው የመዋልና ጉዳያቸውን የማስፈፀምና የተለያዩ መብቶች ተሰጧቸዋል፡፡ እነዚህ አስጠጪዎች የፖለቲካ እስረኞችን በመከታተል ከእነርሱ ጋር የተገናኘን ማንኛውም እስረኛ እየመዘገቡ ወደ ቢሮ ያስተላልፋሉ፡፡ባስተላለፉትም መሠረት እየተጠሩ ዘግናኝ ማስፈራሪያና ድብደባ ይፈፀምባቸዋል፤ በካቴና እጃቸውና እግራቸው እየታሰሩ ለሳምንታትና ለወራት እንዲቆዩ ይደረጋል፡፡
በየሳምንቱ በሚደረግ የቤት ውስጥ ግምገማ ወይም የዞኑ አጠቃላይ ስብሰባ ላይ አሰራራቸውን የሚነቅፍ አስተያየት የሰጠ እስረኛ "አንተ የግንቦት 7 ወይም ኦነግ ነህ" በማለት የሚያሰቃዩት እስረኛ ብዙ ነው፡፡ በቅርቡ ያሬድ ሺፈራው የተባለውን እስረኛ ከግንቦት 7 ሰዎች ጋር ቅርርብ አለህ በማለት በተደጋጋሚ እየጠሩ ሲዝቱበትና ሲያጨናንቁት ከቆዩ በኋላ አንድ ቀን ጠርተው ነገ በሚኖረው ስብሰባ ላይ "የግንቦት 7 አባል ነኝ፡፡ ይህንን ያንን አድርግ ብለውኝ ነበር" ብለህ ተናገርና እንተውሃለን ሲሉት እሺ ብሏቸው ወጣ፡፡ በኋላም በስብሰባው ላይ እንዲነሳና እንዲናገር ሲያደርጉት "እኔ እናቴ ያሬድ ብላ ነው ስም ያወጣችልኝ አሁን ግን እናንተ ግንቦት 7 ብላችሁ ስም አወጣችሁልኝ" ብሎ ሊቀጥል ሲል አስቆሙት፡፡ በኋላም ከዚያ ዞን አንስተው እስካሁን የት እንዳደረሱት አይታወቅም፡፡ እንዲሁም አሸናፊ የተባለ እስረኛ በማንነቱ ብቻ ከቆጠራ በኋላ አስወጥተው ከባድ ድብደባ ፈጽመውበታል፡፡ በተመሳሳይም ዮናስ አስፋው በተባለው እስረኛ ላይም ከባድ ድብደባ ተፈጽሞበታል፡፡ እንዲሁም ብዛት ያላቸው የአማራና የኦሮሞ ተወላጆች ላይ ወከባ፣ ዛቻና ማስፈራሪያ ከፈጸሙ በኋላ 13ቱን የካቲት 22 ቀን 2005 ዓ.ም ወደ ዝዋይ በመጫን እዚያ በሚገኘው የጨለማ ቤት እያሰቃዩአቸው ይገኛል፡፡
እነዚህም፡- 1.ስሜነህ ምትኩ
2.አምባቸው ዘሪሁን
3.አንተነህ አምሮሎ
4.ሰይድ ሁሴን
5.ናደው ፍርዴ
6.ካሳሁን አብደላ
7.ዮርዳኖስ ግርማ
8.ደ/አዝማች በየነ
9.አለነ ብላታ
10.ገብሬ ሲሳይ
11.ዮናስ አስፋው ይገኙበታል፡፡

በህገ መንግሥቱ ላይ "ማንኛውም እስረኛ ለቤተሰቡ ቅርብ በሆነ እስር ቤት እንዲታሰር ይደረጋል" ተብሎ የተቀመጠ ሲሆን እነዚህንና ሌሎች ብዛት ያላቸውን እስረኞች ወደ ዝዋይ የሚጫኑበት ምክንያት ከዘረኝነት የመነጨ ጥላቻቸው መገለጫ ነው፡፡ እነዚህን እስረኞች ከቤተሰቦቻቸው በማራቅ ለማጨናነቅና የሚደርሱባቸውን ተፅዕኖዎች እንዳይታወቁ (ወደ ሕዝቡ እንዳይደርሱ) ከአዲስ አበባ ማራቁ እንደ መፍትሄ ስለሚወሰድ ነው፡፡

**ከግንቦት 7 ጋር በተያያዘ ተከሰው በእስር ቤት ከሚማቅቁት ውስጥ፡**

1.ብ/ጄኔራል ተፈራ ማሞ
2. አሳምነው ፅጌ

ቃሊቲ በሚገኘው የብቻ ማሰሪያ ክፍል ውስጥ 3 ዓመት ከ8 ወራት ሲሰቃዩ ከቆዩ በኋላ ለብዙ ቀናት እጅና እግራቸውን በካቴና አስረውና የቤተሰብ ግንኙነት ከልክለው ወደ ዝዋይ እስር ቤት ጭነዋቸዋል፡፡

በተጨማሪም በተመሳሳይ ክስ ከተከሰሱት ውስጥ፡-

1.ሌ/ኮ ደምሰው አንተነህ
2. ሌ/ኮ ዓለሙ ጌትነት
3. ሌ/ኮ ሰለሞን አሻግሬ
4. ሻለቃ መኮንን ወርቁ

የተባሉትን የካቲት 22 ቀን 2005 ዓ.ም ወደ ዝዋይ ጭነዋቸዋል፡፡ እዚህ አ/አ በሚገኘው ቃሊቲና ቂሊንጦ እስር ቤት ከአንድ ዞን ወደ ሌላ ዞን እንዲሁም ወደ ጨለማ ቤት እያዘዋወሩ ሲያሰቃዩአቸው የነበረ ሲሆን በተደጋጋሚ በተለያየ ጊዜ እየጠሩ "በጥይት እንደበድባችኋለን"፣ "የመጀመሪያው ጥይት እናንተ ላይ ነው የምናሳርፈው" ወ.ዘ.ተ እያሉ ይዝቱባቸው ነበር፡፡ ይህ ሳያንስ ከሚስቶቻቸውና ከልጆቻቸው በማራቅ ዝዋይ በሚገኘው ልዩ ቤት አጉረው እያሰቃዩአቸው ይገኛሉ፡፡

በተመሳሳይም 1.አቶ በቀለ ገርባ
2.አቶ ኦልባና ሌሊሳ

የተባሉ የኦፌኮ/መድረክ አመራሮችን ቃሊቲ በሚገኘው የጨለማና ልዩ እስር ቤት ውስጥ ካሰቃዩ በኋላ ወደ ዝዋይ ጭነው እዚያ ባለው ልዩ እስር ቤት ውስጥ ይገኛሉ፡፡
ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የፖለቲካ እስረኞችንና በማንነታቸው ብቻ የአማራና የኦሮሞ ብሄር ተወላጆችን

ወደ ዝዋይ በመጫን ከቤተሰቦቻቸው በማራቅና በዝዋይም የተለያዩ ጫናዎችን በመፈፀም ላይ ይገኛሉ፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜም ይህን ድርጊታቸውን አጠናክረው እየቀጠሉበት ይገኛሉ፡፡ ምንም እንኳን ለነዚህ ተቋማት ማረሚያ ቤት የሚል ስም የሰጧቸው ቢሆንም እውነታው ግን ከዚህ በፍፁም የተለየ ነው፡፡ አንዳችም የማረምና የማነፅ ተግባር የሚካሄዱባቸው ተቋማት አይደሉም፡፡ ይልቁንም ከተቆራኛቸው የዘረኝነት አባዜ በመነጨ እስረኞችን በማንነታቸውና በፖለቲካ አቋማቸው በእስር ቆይታቸው ማጨናነቅ፣ ማዋከብ፣ አየጠሩ ማስፈራራት፣ ቤተሰቦቻቸው ላይ ጫና መፍጠር፣ ከቤተሰቦቻቸው በማራቅ ግንኙነታቸውን ማዳከምና ከተቻለም ማቆራረጥ እንደ ፖሊሲ ይዘው እየተገበሩት ይገኛል፡፡

ከግንቦት 7 ጋር በተያያዘ የታሰሩት እስረኞች ከቤተሰብ ጋር በሚገናኙበት ወቅት የህወሓት አባላት የሆኑ ፖሊሶች ብቻ ተመርጠው ከጎናቸው ስለሚቆሙና ለደቂቃም ያህል ስለማይለዩ ቤተሰባዊ ሚስጥሮችን(ጉዳዮችን) እንኳን ለማውራት አስቸጋሪ ነው፡፡

በጭውውት ውስጥ መንግስትን ይነካል የሚሉት አረፍተ ነገር ከሰሙ ዛቻውና ማስፈራሪያው ይህ ነው የሚባል አይደለም፡፡ በእስር ቤቱ የሚሰጡ ማንኛውንም አገልግሎቶች (ዝውውር፣አመክሮ፣ይቅርታ፣የፍ/ቤት ጉዳዮች፣ልዩ ልዩ ወ.ዘ.ተ) ለማግኘት ማንነትህ ወሳኝ ነው፡፡ ወይ የነሱ ሰው መሆን አለብህ ካልሆነ ደግሞ ገንዘብ በደንብ ሊኖርህ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ እስር ቤት ውስጥ ዘግናኝ የሆነ የሰብዓዊ ጥሰት ያለበት፣ በማንነቱ ብቻ እስረኛው ቁም ሥቃዩን የሚያይበት ቦታ ነው፡፡ ሰውን ማሰር ብቻ ሳይሆን አሥረውም ካላሰቃዩ ካላንገላቱ እርካታ የማይሰማቸው ዘረኞች የበዙበት እስር ቤት ነው፡፡

ዓላማቸው ከእነርሱ ውጭ ያሉ ሕዝቦችን በእስር በማሰቃየት ቢቻል መግደል ካልሆነም በቁሙ መግደል ነው፡፡ የሚገርመው ደግሞ የሚቆጣጠራቸው አካል ያለመኖሩ ነው፡፡ ለስሙ ከፌ/ማ/ቤ ኮሚሽን እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ነን ባዮች ነገር ግን ከራሱ ከመንግስት በላይ ለመንግስት የሚቆረቆሩ ካድሬዎች የሆኑ የእነ ፓስተር ዳንኤል ገብረ ሥላሴ አይነት ድርጅቶች ለተለያየ ጊዜ እስር ቤቱን ቢጎበኙም ከተቆርቋሪነታቸው የተነሳ እስር ቤቱን አድንቀውና አወድሰው ከመሄድ ባለፈ እውነታውን ማወቅም ሆነ ማሳወቅ አይፈልጉም፡፡

ችግራችንን የሚያይልንና መፍትሄ የሚሰጠን አካል ባለማግኘታችን ይኸው ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ስቃያችንን እንዲያውቅልን ስንል እውታውን በጥቂቱም ቢሆን ልናሳውቅ ተገደናል፡፡

# የሞጆ ነዋሪዎቿን ያለ ካሳ እየተፈናቀሉ ነው

በሰሜን ምስራቅ ሸዋ ዞን የምትገኘው ሞጆ ከተማ በ1915 ዓ.ም አዲስ አበባን ከጅቡቲ በባቡር ለማገናኘት በማሰብ ከድሬዳዋ እስከ አቃቂ የሚደርስ መስመር እንዲዘረጋባትና የባቡር ጣብያ እንዲገነባባት ተደርጋለች ፡፡ ይህንንም ተከትሎ ሞጆ ከሌሎች ከተሞች ቀደም ብላ ከእንቅልፏ በመባነን የቴሌግራፍ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆናለች፡፡ የባቡር መንገደኞችን የሚያስተናግዱ ሬስቶራንቶች ሞጆን ደማቅ መስላ እንድትታይ ትልቅ የሚሰኝ አስተዋእጾ አበርክተዋል፡፡

በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ የተዘረጋውን የባቡር መስመር በአዲስ መልክ ለመገንባት የምድር ባቡር ድርጅት በአሁኑ ወቅት እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ከቻይና ኩባንያዎች ጋር በመተባበር የባቡር ጣብያውን ለመገንባት የሚያስችልና መስመሩ የሚዘረጋበት ቦታ ርክክብ ተፈጽሞ የመጀመሪያ ደረጃ ስራ እየተሰራ ነው፡፡

የከተማው አስተዳደር በልማቱ ምክንያት ለሚፈናቀሉ ዜጎች በግልጽ በህግ የተቀመጡትን መብቶቻቸውን የማስከበር ግዴታ ያለበት ቢሆንም በካሳ ክፍያ፣ በተተኪነት በሚሰጥ መሬት፣ ነዋሪዎችና በግብርና ይተዳደሩ ለነበሩ ገበሬዎች ንብረታቸውን ለማዘዋወር የሚያስችላቸውን የ90 ቀን ጊዜ ባለመስጠት በደል ስለ መፈጸሙ የደረሰንን መረጃ ለማጣራት በማድረግ ሁለት የፍኖተ ነጻነት ጋዜጠኞች ወደ ሞጆ አምርተው ነበር፡፡

ከ60 ሺህ ካሬ ሜትር በላይ በመያዝ ገበሬዎችን በመቅጠር በእርሻ ስራ ይተዳደሩ የነበሩ የአካባቢው ነዋሪዎች የእርሻ ቦታቸውን እንዲያስረክቡ በመደረጋቸው የነገን ህይወት ፈርተዋል፡፡ ሰፊ የእርሻ መሬት ከነበራቸው ገበሬዎች መካከል አንዱ ‹‹ከ40 ዓመት በላይ የኖርነውና ቤተሰብ የመሰረትነው በግብርና ሞያ ነው፡፡ የእኛ ህይወት ከከብቶችና ከመሬት ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ ቀሪውን የህይወት ዘመናችንንም በዚህ መልኩ የማሳለፍ ውጥን ነበረን፡፡ እኛ ልማቱን አንቃወምም፡፡ ምክንያቱም ለአመታታት ስንሰራ የነበረውም ሞጆን ለማልማት ነበር፡፡ ጥያቄያችን ከተማው የሚለማው ለማን ነው? የሚል ነው፡፡

ለእኛ ከሆነ የሚለማው እኛ እንደ አሮጌ ዕቃ የትም መወርወር የለብንም፡፡ በህጉ መሰረት ተገቢው ካሳ ተከፍሎን፣ ተመጣጣኝና ተቀያሪ ቦታ ሊሰጠን የሚገባን ቢሆንም ካሳው አልተከፈላቸውም ላለማለት ያህል የተፈጸመ ብቻ ነው፡፡ በብሎኬት ለተገነባ የእህል ማከማቻ ጎተራ ሃያ ሺህ ብር እንከፍላለን ይላሉ፡፡

ነገር ግን ይህ ብር የጭቃ ቤት እንኳን መስራት የሚያስችል አይደለም፡፡ ከሁሉም በላይ ለግብርና ከ50ሺህ ካሬ ሜትር በላይ የነበራቸው ገበሬዎች መሬቱን ለልማት ተነጥቀው የተሰጣቸው ልዋጭ ቦታ ከ160ካሬ አይበልጥም፡፡ ይህ ልዋጭ ቦታ ገበሬውን ወደ ስራ መልሶ የማያስገበው በመሆኑ በካሳ ክፍያ ስም የተሰጠችውን ገንዘብ በልቶ ዛሬ የጉልበት ሰራተኛና ሎተሪ አዟሪ ለመሆን ተገድዷል›› ይላሉ፡፡

ቤቶቻቸው ወይም የግብርና ይዞታቸው በልማት ስም ለሚነሳባቸው ሰዎች የመዘጋጃ 90 ቀን መስጠትና የሚነሱበትን ምክንያት በዝርዝር ምክንያት በመግለጽ ይፋዊ ደብዳቤ መስጠት ያለበት ቢሆንም በሞጆ ይህ አለመደረጉን ነዋሪዎቹ ይናገራሉ፡፡ አንዳንዶቹም ‹‹የተሰጠን ግዜ የ15 ቀን ብቻ ነበር፡፡ ይህ እንዴት ይሆናል በማለት ከእኛ መሃል ፍርድ ቤት በመሄድ ቤታቸው እንዳይፈርስባቸው እግድ ያወጡ ሰዎች ነበሩ ፡፡ ነገር ግን የፍርድ ቤቱ እግድ አፍራሽ ግብረ ሃይሉን አላገደውም፡፡ቤቱን አፍርሰው ሄደዋል፡፡ ሌላው ቀርቶ አንዲት ገበሬ የአባቷ ለቅሶ ላይ በተቀመጠችበት ሁኔታ ቤቷን አፍርሰውባታል፡፡ ከዚህ በፊትም የ6 ቀን አራስ በተኛችበት መጥተው መኖሪያዋን እንዳልነበር አድርገውታል፡፡ አራሷ ህጻን ልጇን ለማዳን በማሰብ ሌላ ንብረቷን ትታ ወጥታለች፡፡ የተፈጸመው ግፍ እጅግ በጣም ብዙ ነው፡፡ ለምሳሌ ለባቡር ጣብያው በማለት ብዙ ሺህ ካሬ መሬት እንዲለቅ አድርገዋል፡፡ ለጣብያው የሚያስፈልገው መሬት ምን ያህል እንደሆነ ብንጠይቃቸውም ሊነግሩን ፈቃደኞች አይደሉም፡፡ በመጀመሪያ የሰጋነው ነገር አልቀረም ለጣብያው ያስፈልጋል በማለት ባስለቀቁን መሬት ላይ ሌሎች ሰዎች የመኖሪያ ቤቶችን ለመስራት ድናጋይ እያፈሰሱ ይገኛሉ፡፡ የእኛን ቤት አፍርሰው ለሌሎች ቤት መስሪያነት መስጠታቸውም በልማት ስም ወንጀል እየተፈጸመ ለመሆኑ ማሳያ ነው፡፡›› ይላሉቅሬታ አቅራቢዎቹ፡፡

ተፈናቃዮቹ የነገሩንን በመያዝ የከተማውን ከንቲባ አቶ ፉፋን አነጋግረናል፡፡ በቅርቡ የከንቲባነቱን ሹመት እንዳገኙ የሚገልጹት አቶ ፉፋ ‹‹የተባለው ሁሉ ውሸት ነው፡፡ ይህን የሚያስወሩትም ልማቱን ማደናቀፍ የሚፈልጉ ሀይሎች ናቸው፡፡›› በማለት የተለመደውን የመንግስትን ማስተባበያ ይሰጣሉ፡፡ አክለውም ‹‹ተገቢውን ክፍያና ተመጣጣኝ የሆነ ቦታም ለተነሺዎቹ እየሰጠን ነው›› ቢሉም እኛ በከተማዋ ተዘዋውረን እንደተመለከት ነው ካሳ ያልተከፈላቸው፣ ተመጣጣኝ የካሳ ዋጋ ያልተተመነላቸውን የከተማዋ ነዋሪዎች እሮሮና አንባ ተመልክተናል፡፡

የምድር ባቡር ድርጅት በጉዳዩ ላይ ያለውን አስተያየት ለማካተት ያደረግነው ጥረት የሚመለከታቸው ሀላፊዎች ባለመገኘታቸው ለጊዜው አይተሳካም፡፡

# “ህወሓት የአማራ ፖለቲከኞችን ከኢትዮጵያዊ ብሔረተኝነት ርዕዮተአለም እንዲወጡ ማድረግ ይፈልጋል”

## ጃዋር መሀመድ የፖለቲካ ተንታኝ



የዛሬው የፍኖተ ነፃነት እንግዳ ወጣቱ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁርና ተንታኝ አቶ ጃዋር መሀመድ ነው፡፡ ከጃዋር መሀመድ ጋር ያደረግነውን ቆይታ በሁለት ክፍል አዘጋጅተነዋል መልካም ንባብ

**ፍኖተ ነፃነት፡- ኢህአዴግ የብሔር ጥያቄ መልሻለሁ ይላል፤ ሆኖም ብሔርን መሰረት ያደረጉ በደሎች ሲፈፀሙ ይታያል፡፡ በርግጥ የብሔር ጥያቄ ተመልሷል ማለት ይቻላል?**

ጃዋር፡- እንደምታውቀው የብሄር ጥያቄ ሁለት አይነት መልስ ነበር የሚያስፈልገው፡፡ አንደኛ እራስን በራስ የማስተዳደር፣ በራስ ባህል ላይ፣ በራስ አከባቢ ላይ ራስንችሎ ማስተዳደር ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የጋራ ሀገርን በጋራ ማስተዳደር፣ ማለትም እንደሀገር በጋራ ያፈሩትን በጋራ የመጠቀም፣ በጋራ ተካፍሎና ተቋድሶ መኖር ነው፡፡ ይህ ማለት የሀገሪቷን ኢኮኖሚ፣የሀገሪቷን ስልጣንና ባህላዊ እሴቶች በጋራ እያዋጡ በጋራ ተቋድሶ መኖር ማለት ነው፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ በርግጥ በተወሰነ ደረጃ ብሔሮች ክልላቸውን እንዲያስተዳድሩ ተደርጓል፤ ያም ቢሆን የተሟላ አይደለም፡፡ ምንም እንኳን የአካባቢው ሰው ሊቀመንበር፣ የወረዳ አስተዳዳሪ ይሁን እንጂ እውነተኛ ስልጣን የለውም፡፡ አንደኛ በህዝብ አይመረጥም፤ በእውነተኛ ምርጫ ስለማይመረጥ እውነተኛ የህዝብ ተወካይ አይደለም፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ከተሾመም በኋላ ቢሆን ታአማኒነቱ ከላይ ስልጣን አፍነው ላሉት ለህወሐቶች ስለሆነ እውነተኛ ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ለብሔሮች አልተሰጠም፡፡ ፈፅሞ ግን የሌለው በጋራ ተካፍሎና ተቋድሶ የመኖር (shared rule) የሚባለው ነው፡፡ እንደሚታወቀው ፌደራል መንግስቱ ሙሉ ለሙሉ በህወሐቶች ቁጥጥር ስር ነው፡፡ ወታደሩ ሙሉ ለሙሉ፣ ደህንነቱም እንደዛው፣ በኢኮኖሚውም፣ በውጪ ጉዳይ የአንድወገንና የአንድ ፓርቲ የበላይነት ያለስለሆነ የብሔር ጥያቄ ተደባብሶ፣ እንደውም ወደባሰ ሁኔታ እየገባ ያለበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ የፌደራል ስርአቱ ምንም እንኳን ለብሔሮች ባህላዊ አይነት መብቶችን ቢሰጥም እነዛን እሴቶች ራሳቸው በሚፈልጉበት መልኩ እንዳያሳድጉ የፖለቲካ ስልጣኑ ስላልተሰጣቸው፣ ማንነት እየከረረና እያደገ ሆኖም ግን እነዛ የማንነት መገለጫዎች በፖለቲካውና በኢኮኖሚው ውድድር ውስጥ ስለማይገቡ ለሀገራችን አደጋ እየጋረጠ ያለበት ሁኔታ ነው የሚታየኝ፡፡

**ፍኖተ ነፃነት፡- በቅርቡ አማርኛ ተናጋሪዎችን የማፈናቀ ዘመቻ ተጀምሯል፤ ድርጊቱ ምን አይነት የፖለቲካ ቀውስ ሊያመጣ ይችላል?**

ጃዋር፡- ወደ ትልቁ ሀገራዊ ጉዳይ ሳንገባ ግለሰቦቹ(ተፈናቃዮቹ) ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ማሰብ ያለብን ይመስለኛል፤ እንደምታውቀው በሀገራችን ከፍተኛ የሆነ የኑሮ ውድነት አለ፣ እንኳን ያረሰውንና ቤቱ ያለውን እህል ጥሎ ወደ ሌላ ሀገር መሰደድ ይቅርና ሰዉ ልጆቹን መመገብ የተቸገረበት ሁኔታ እያለ፣ ሰውን ከቤቱ ማፈናቀል ዶፍ ዝናብ ባለበት ሁኔታ ሰውን ከቤቱ እንደማስወጣት ነው የሚታየኝ፡፡ በዜጎች ላይ እየደረሰ ያለው መፈናቀል በጣም ያሳስበኛል፡፡ በጣም የሚያሳዝነውና አፅንኦት ሊሰጠው የሚገባው ይሄ ይመስለኛል፡፡

**ፍኖተ ነፃነት፡- አማርኛ ተናጋሪዎችን የማፈናቀሉ አላማ ምን ሊሆን ይችላል?**

ጃዋር፡-ይሄ ተግባር ለምን አላማ ተፈፀመ የሚለው፣ እንዳለመታደል ሆኖ ሀገራችን ላይ የሚመጡ መንግስታት ዜጎችን እንደሰዎች ሳይሆን ለፖለቲካ ስራ እንደተፈጠሩ ዕቃዎች ነው የሚያዩት፤ አሁን እያረጉ ያሉት ከደቡብና ከቤንሻንጉል ክልሎች ወደ ፊትም ከሌሎች ክልሎች በአማራ ተወላጆች ላይ የሚያደርጉት መፈናቀል የፖለቲካ አላማ እንዳለው ግልፅ ነው፡፡ አንደኛ በአማራውና በሌላው ብሔረሰብ መሀከል ተስማምቶና ተቻችሎ አብሮ ለዴሞክራሲና ለእኩልነት እንዳይሰራ በብሔሮች መሀከል ሁል ጊዜ መጠራጠር ግጭትና ቁጭት እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡ ይሄ እንግዲህ ላለፉት 21 አመታት በደንብ ያየነው ጨዋታ ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ህወሐት የአማራውን ማህበረሰብ በመንካት የአማራ ፖለቲከኞችን ከኢትዮጵያዊ ብሔረተኝነት ርዕዮተአለም እንዲወጡ ማድረግ ይፈልጋል፡፡

**ፍኖተ ነፃነት፡- ፌደራሊዝሙ ብሔር ላይ ያተኮረ መሆኑ ነው እንዲህ አይነቱ የዘር ማንነት ላይ ያተኮረ በደል እንዲፈፀም ያደረገው የሚሉ አስተያየቶች ይደመጣሉ**

ጃዋር፡- ይሄ የኤትኒክ ፌደራሊዝም የፈጠረው ነገር አይመስለኝም፡፡ ኤትኒክ ፌደራሊዝሙ ችግር ፈጠረ ቢባል፣ የቤንሻንጉል ህዝብ ተነስቶአማራ ከክልላችን ይውጣ ብሎ ቢጠይቅ፣ በቤንሻንጉል ህዝብ ውስጥ ፀረ አማራ አመለካከት ቢድግ ኖሮና ህዝቡ አማራውን ከክልላችን ውጣ ቢለው የኤትኒክ ፌደራሊዝም ችግር ነው ትለዋለህ፤ ይሄ እኮ በፌደራል መንግስት ውሳኔ እተሰራ ያለ ስራ ነው፡፡ ቤንሻንጉል ሄደህ ተወላጆቹን ስለአማራ መፈናቀል ብት ጠይቃቸው አያውቁትም ልክ እንደኔና እንዳንተ ከሬዲዮ ነው የሚሰሙት፡፡ እኔ ወደ ስፍራው በመደወል ጉዳዩን ለማጣራት ሞክሬያለሁ፡፡ በርግጥ ፌደራሊዝሙ ሲቋቋም ምንም እንኳን የተወሰኑ ጥቅሞች ቢኖሩትም፣ ለህውሐት ህዝብን የመከፋፈል ሴራ እንዲያመች ተደርጎ መሆኑ ምንም ጥያቄ የለውም፡፡ ሆኖም ፌደራሊዝሙ ባይኖርም ይሄን ማድረግ ይችላል፡፡ በነገራችን ላይ ከህውሐት በፊት የነበሩትም መንግስታት ህዝብን እንደእቃ የመቁጠር ከሰሜን አንስቶ አማፂ ነው ወደ ሚሉት ወደ ደቡብ የማስፈር ነገር ነበራቸው፡፡ ለምሳሌ እንደቀድሞው እንደደርግ ቢሆን “ለምን ከጎንደር መጥተህ ጎጃም ገባህ” ብሎ መመለስ ማለትእኮ ነው፡፡ ፌደራሊዝሙን ባዋቀረው ህገመንግስት ውስጥ ማንኛውም ዜጋ በፈለገው ክልል ውስጥ እንደፈለገው መስራት እንደሚችል ይገልፃል፡፡ የእያንዳንዱ ክልል ህግም እንደዛ ነው የሚለው፡፡ አንድ ክልል ውስጥ ለመኖር የግድ የዛ ክልል ተወላጅ መሆን የለብህም፤ በየትኛውም ክልል ውስጥ መኖርና መስራት ትችላለህ፡፡

ስለዚህ ገገርዎቹ ሆነ ብለው ህዝብን ለማጋጨት ፣ህዝብን ለማሰቃየትና የፖለቲካ ባላንጣችን ናቸው የሚሏቸውን አካላት የሚያደርጉት ጨዋታ እንጂ ብዙም ከፌደራሊዝሙ ጋር የተያያዘ አይመስለኝም፡፡ ፌደራሊዝሙ ላይ ስናተኩር እርነተኛን የችግሩን ምንጭ እንዳናጣው እሰጋለሁ፤ እውነተኛው ምክንያት የገገርዎቹ ተንኮልና ደባ ነው፡፡ በታሪካዊ ሂደት አማራው በሁሉም ክልል አለ፤ ሆኖም እስከ አሁን የየክልሉ ህዝብ ተነስቶ አማራ ይውጣልኝ ሲል

አላየሁም፡፡ ህወሐት የአማራን ህዝብ የሚነቅለውና የሚተነኩሰው ህዝቡ ጋር ለማጣላት ነው፡፡ ከዚህ በፊትም ሌላው ህዝብ ግጭት የነበረው በአማራው ህዝብ ስም ህዝብን ከሚጨቁኑ መንግስታት እንጂ ከአማራው ጋር አልነበረም፡፡

**ፍኖተ ነፃነት፡- የማፈናቀል ዘመቻው በህዝቦች መካከል የሚፈጥረውን ችግር እንዴት ትገልፀዋለህ?**

ጃዋር፡- እንግዲህ በአጭር ጊዜ ከመሀል ሀገር ርቀው በሚገኙ አካባቢዎች ባሉ ማህበረሰቦች መሀከል በፊት የነበሩትንና አዳዲስ ቁርሾዎችን ሊፈጥር እንደሚችል እሰጋለሁ፡፡ በከፍተኛ ደረጃ ግን እንደዛ ብሔሮችንና ማህበረሰቦችን በሃይማኖት ይሁን በብሔር እያጋጩ መሄድ ኢትዮጵያ ውስጥ እያለቀለት ያለ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ከዚህ በፊት ተደጋግሞ ያየነው ፊልም ነው፤ አንዱ ላይ ሲሰራ ቁጭብለን እናየው ነበር፤ እውነት ይመስለን ነበር፤ በኛም ላይ ሲደጋገምና ተደጋግሞ ስለቀረበ ሰዉ እንደዱሮው መታለል ያቆመበትና ለሚደርሰው የሰብአዊ መብት ጥሰትና ግፍ "የእከሌ ቡድን አደረሰው፣ የእከሌ ማህበረሰብ አደረሰው" ከማለት ባለፈ መንግስትን ተጠያቂ ወደ ማድረግ የገባበት ሂደት ያለ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ተመልከተው አሁን ቤንሻንጉል ውስጥ የክልሉ ሰው፣ የወረዳው ሰውና ገበሬው ነው ያፈናቀላቸው እንዳይባል፣ ፌደራል መንግስት ማስቆም ይችል ነበር፡፡ የማፈናቀል ተግባሩ ከተጀመረ አንስቶ ሁለት አመት የፈጀ ነው፤ ፌደራል መንግስት ስምምነት ባይኖር ኖሮ ይህን ማስቆም ይችል ነበር፡፡ አለማስቆሙም የሚያሳይህ ማፈናቀሉ የፌደራል መንግስቱ አላማ መሆኑን ነው፡፡ ህዝቡ የፌደራል መንግስት ድንቅ እጅና የህወሐት ሰዎች ሴራ እንደሆነ ገብቶታል፡፡ የቤንሻንጉል ሰዎችን ከመኮነን ይልቅ እውነተኛው ስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ተጠያቂ ወደ ማድረግ ገብቷል፡፡ በሙስሊሞቹም ደረጃ ብታየው በፊት በክርስቲያኑ ላይ እንዲያነጣጥሩ ስሞከር የነበረው፡፡ ሆኖም ጥፋተኛ የሆነው ማን እንደሆነ በግልፅ ታውቆ ሙሉ ለሙሉ በመንግስት ላይ ያነጣጠሩበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ ይህ የሚያሳየን በሀገራችን የመብት ትግል ውስጥ ለውጥ እየመጣ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ በፊት እርስ በርስ መፋጠጥ ነበር፤ አሁን ግን እውነተኛ ጨቋኝ በሆነው ስርአት ላይ ማፍጠጥ ተጀምሯል፡፡

**ፍኖተ ነፃነት፡- መንግስት እየፈፀመ ያለውን የማፈናቀል ዘመቻ በተመለከተ ምን መደረግ አለበት?**

ጃዋር፡- የአማራ ህብረተሰብ ሲነካ የአማራ ልሂቃን መናገራቸው ትክክል ነው፤ ግን ለእነሱ ብቻ መተው ያለበት ስራ አይደለም፤ አማራ ያልሆነ ዜጋም ሊቃወመው ይገባል፡፡ አንደኛ የማፈናቀሉ ተግባር የሰብአዊ መብት ጥሰት ነው፤ ማንኛውም ሰው እንደዚህ አይነት ዘግናኝ ተግባር መቃወም አለበት፡፡ ሁለተኛ ደግሞ በሀገርና በህዝብ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን አደጋ ሁሉንም ሊያዳርስ የሚችል ነው፡፡ ዛሬ አማራው ተጠቃ ነገ ሌላው ይጠቃል፡፡ ያም ብቻ ሳይሆን በአማራና በቤንሻንጉል ማህበረሰብ መሀከል ቁርሾ እየበዛ ከሄደ በእነሱ መሀከል የሚፈጠረው ግጭት በአካቢያቸው ያለው ሌላ ህብረተሰብ ላይም የሚያደርሰው ጉዳት ከፍተኛ ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ተግባሮች መደገም የለባቸውም፡፡ ሶስተኛ ዛሬ አማራው ሲጎዳ ዝም ብለን የምናይ ከሆነ ሌላው ሲበደል ደግሞ አማራው ቁጭብሎ የሚያይበት ሁኔታ ስለሚኖር አደገኛ ሁኔታ ይኖራል፡፡ እንደውም አማራ ያልሆንን ልሂቃን ማፈናቀሉን በግንባር ቀደምትነት ወጥተን መቃወም ይገባናል፡፡ አማራው እኛ ከጎኑ እንዳለን ሲያውቅ እንደ ኢትዮጵያዊነትና እንደ ሰው ልጅነት በህዝቡ መካከል ያለው መተሳሰብና መፈቃቀር እየጨመረ ይሄዳል ብዬ ነው የማስበው፡፡ አማራ ያልሆነው ማህበረሰብ ለአማራው ድምፅ ሆኖ መውጣት አለበት፡፡ ኦሮሞው ሲጎዳ ኦሮሞው ብቻ የሚናገር ከሆነ፣ አማራው ሲጎሳ አማራው ብቻ የሚቃወም ከሆነ ሁላችንም በየፊናችን ተከፋፍለን የምንቀርበት ሁኔታ ነው የሚኖረው፡፡ ሀዲያ ሆንክ ከንባታ ሆንክ ሺናሻ ለዚህ ህዝብ መናገር አለብን፡፡ ይህ ሲባል ግን የአማራ ተወላጆችም በወገኖቻቸው ላይ በደረሰው ጥቃት መቆጣት መቃወም አለባቸው፤ ይሄ ተገቢ ነው ይህን በማድረጋቸው መኮነን የለባቸውም፡፡ ማህበራትም ሆኑ በጎፈቃደኛ ግለሰቦች እነዚህ የተፈናቀሉ ዜጎች መጉላላት እንዳይደርስባቸው የነብስ አድን ጥሪ በማድረግ ድጋፍ ሊያደርጉላቸው ይገባል፡፡ ወደ ቀድሞ ስፍራቸውም ሲመለሱ በተቻለ መጠን በፍጥነት እንዲቋቋሙ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ሌላው እንዲህ አይነት ወንጀል እንዳይደገም መንግስት ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ ማድረግ አለብን፡፡ እንዲህ አይነቱ ወንጀል በሌላ ቦታም እንዳይደገም ለመፈናቀሉ እንዳይደገም ማድረግ የሚያስፈልግ ይመስለኛል፡፡ በሌላ ደረጃ ግን በሰው ልጅ ላይ ያነጣጠረ ወንጀል እንዲቆም መንግስት ላይ ጫና ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**ፍኖተ ነፃነት፡- ከኢህአዴግ አባል ድርጅቶች አንዱ የሆነውና አማራን እወክላለሁ የሚለው ብአዴን በአማርኛ ተወላጆች ላይ የሚደርሰውን በደል በዝምታ መመልከቱ ምን ያሳያል?**

ጃዋር፡- እውነቱን ለመናገር ብአዴንን ስታየው የአማራ ድርጅትም አይደለም፡፡ በተለይ የድርጅቱ ቱባ ባለስልጣናት የአማራ ተወላጆች አይደሉም፤ ከህወሐት ጋር በደምና በጥቅም የተሳሰሩ ናቸው፡፡ የአማራ ተወላጅ የሆኑትም እውነት የአማራን ህዝብ መብት ለማስከበር የሚችሉ፣ የህዝቡ ውክልና ያላቸው ሳይሆኑ ለእንጀራቸው እዛ ውስጥ ያሉ ናቸው፡፡ ብአዴን የአማራን ህዝብ ጥቅም ያስከብራል፣ የአማራ ህዝብ ይከላከላሉ ብሎ መጠበቅ ራስን ማታለል ይመስለኛል፡፡

የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ብሄር ድርጅት ይባሉ እንጂ እውነተኛ ስልጣን ላይ ላለው አካል አገልጋዮች ናቸው፡፡ ኢትዮጵያን እንደኩባንያ ከወሰድካት ህውሐት የኩባንያው ባለቤት ነው፡፡ እነብአዴንና ኦህዴድ የኩባንያው ሰራተኞች ናቸው፡፡ አይደለም እንወክለዋለን የሚሉትን ህዝብ መብት ሊያስከብሩ /እንደግለሰብ/የራሳቸውን መብትም ማስከበር የሚችሉ ድርጅቶች አይደሉም፡፡

በነገራችን ላይ ኦሮሚያ ውስጥ የሚፈፀም ብዙ ብዙ ግፍ አለ፤ በአሁኑ ወቅት ከ25 ሺህ በላይ የኦሮሞ ተወላጆች በየእስርቤቱ ይሰቃያሉ፡፡ ኦህዴድ አንድ ቀን፣አንድ ቀን ስለዚህ ተናግሮ አያውቅም፤ ታሳሪዎቹ በአካባቢያቸው የመዳኘት መብታቸው እንኳን አይከበርም፣ ፌደራል መንግስት ነው ጉዳያቸውን የሚያየው፤ ይህን አይነቱን ግልፅ ህገመንግስት ጥሰት ኦህዴድ እንቢ ማለት አይችልም ፤ ኦህዴድ ሳይችል አሁን ብአዴን ስለአማሮች መፈናቀል የሆነ ነገር ያደርጋል ብሎ መጠበቅ አይቻልም፡፡ እነዚህ ፓርቲዎች እንወክለዋለን የሚሉትን ህዝብ አይወክሉትም፡፡ አንድ ድርጅት ህዝብን እወክላለሁ ሲል ከህዝቡ ውስጥ የወጣና የራሱ ኑሮ በህዝቡ ላይ የተንጠለጠለ ሲሆን ነው፡፡ እነዚህ ፓርቲዎችና በተለይ አመራሩ ከህዝቡ የወጡ አይደሉም፤ ህዝቡ አይደለም ስልጣን ላይ ያወጣቸው፣ ስልጣን ላይ ያወጣቸው ህወሐት ነው፡፡ ስለዚህ አገልግሎት የሚሰጡት፣ ተአማኒነታቸውም፣ የሚያስፈፅሙትም የህወሐትን ጥቅም ማስከበር ነው፡፡

ስለዚህ ብአዴኖች ከጉራፈርዳም ሆነ ዛሬ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ስለተፈናቀሉ የአማራ ተወላጆች አስመልክቶ በግል ሊቆጫቸው ይችላል፣ ግን አንድ እርምጃ እንወስዳለን ካሉ የህወሀትን ፖሊሲ መቃወም ነው የሚሆንባቸው፤ የህወሐትን ፖሊሲ መቃወም ደግሞ የራሳቸውን ማጋለጥ ስለሚሆን ሆዳቸውን እየቆጫቸውም ቢሆን ዝም የሚሉበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ አንዳንዶቹ ግን ቅድም እንዳልኩህ የአማራ ተወላጆችም ስላልሆኑ በደሉ ላይሰማቸውና ደንታም እንደማይሰጣቸው ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ከብአዴን መጠየቁ አግባብ ነው ሆኖም ከብአዴን መፍትሔ መጠበቅ አግባብ ያለው አይመስለኝም፡፡

**ፍኖተ ነፃነት፡- መንግስት ዜጎችን እያፈናቀለ መሬታችንን ለባእዳን መሸጡ ምንአንድምታ አለው ?**

ጃዋር፡- አሁን አማራ ላይ ያተኮሩበት የራሳቸው አላማ ስላላቸው ስለአማራው እናወራለን እንጂ ጋንቤላዎች፣ ቤንሻንጉሎች፣ ኦሮሞዎች ከመሬታቸው ላይ በሚሊዮኖች እየተፈናቀሉ መሬታቸው በርካሽ ለህንዶችና አረቦች እና ለተለያዩ ሀገርዜጎችና ኩባንያዎች እየተቸበቸበ ነው፡፡ ጋንቤላ ውስጥ የተሰራውን ዶክመንታሪ አይተኸዋል፤ ሌላው ሳጥቀር የኦሮሞ ባህላዊ ማዕከል የሆነውን ኦዳን ሳይቀር እየቀነቃቀሉት ነው፡፡ አንተካለህበት ወደ ቡራዩ ወደ ሰበታ ወጣ ስትል ህዝቡ የለም በሰላምጤፍ አምርቶ ይኖር የነበረው ማህበረሰብ ዛሬ የቀን ሰራተኛ ሆኖ ድንጋይ ይፈልጣል፡፡ ለምን ቢባል መሬቱን አፈናቅለው ሸጠው ብሩን ወደ ኪሳቸው ለመክተት፡፡ መንግስት በህገመንግስቱ መሬት የማስተዳደር እንጂ የመሸጥ መብት በህገመንግስቱ አልተሰጠውም፡፡ በጋንቤላና በተለያዩ ክልሎች የሚደረገው መሬት ጠመቸብቸብ ተግባር ህገወጥ ነው ፤ ለዛውም እጅግ በረከሰ ዋጋ ለነገሩ የኢትዮጵያ መንግስት ለዜጎች ደንታ የለውም ምክንያቱም በዜጎች የተመረጠ ስላልሆነ፡፡ በተለይ ይህን ስርአት ጠሚመሩት በግልፅ ሀብት ለማካበት ሌላውን ጠሚቦጠቡጡ ናቸው፡፡ በግልፅ ይሄን እያደረጉ ነው፡፡ አምና ለበአዶች መሬት የተቸረቸረውን ቁጭብለህ ብታሰላው ኢትዮጵያ በ50 አመት የምገኘውን የሀገራችን ገበሬዎች አስፈላጊው ግብአት ከቀረበላቸው በአንድ አመት ያስገቡታል፡፡ እነዚህ መሬት አጥተው የሚንከራተቱ ዜጎች በአግባቡ መሬት ቢሰጣቸውና በአመቺ ፖሊሲና ግብአት ቢደገፉ በአንድ አመት ሀገር የሚያሳድጉ ናቸው፡፡ ችግሩ ግን ስልጣን ላይ ያሉት ሰዎች ስለ ሀገር አይደለም የሚያስቡት፤ የኢኮኖሚ እድገት እያሉ ቁጥሩን ጨማምረው በዛው ኪሳቸውን የመሙላት ነው፡፡ ለነገሩ የሀገራችን ዜጎች ከአመት አመት ከድርቅ ካልተላቀቁና እርዳታ ከመንግስት እጅ የሚጠብቁ ከሆነ በህዝቡ ላይ አጠቃላይ ቁጥጥር ማድረግ ያስችላቸዋል፡፡ ስርአቱ ከአወቃቀሩም ዜጎችን የማስቸገር እንጂ ዜጎችን የመርዳት አላማ የለውም፡፡ መሬት ለበአዶች ከመቸብቸብ ዜጎች ከአንዱ ክልል ወደ ሌላ ክልል ሄደው የሚሰፍሩበትን መንገድ ተወያይቶ መቀየስ ይቻል ነበር፡፡ ሆኖም ዜጎችን ሳይዘጋጁበት ድንገት ማፈናቀሉ የራሱ የፖለቲካ አላማ አለው፡፡

**ፍኖተ ነፃነት፡- ቀጣዩ ክፍል ሳምንት ይቀርባል**

# አገሬን የምትል በየት አለህ ?

**ዳዊት ስለሞን**

ጥቃት የመጨረሻው ጥግ ሲደርስ የጥቃቱ ሰለባዎቸ የሚያነሱት ጥያቄ “አገራችን የት ነው” የምትል ስለ መሆኗ የአዲስ ነገር፣የአውራምባ ታይምስና የሙስሊሞች ጉዳይ መጽሄት አዘጋጆችን ማስታወስ ብቻ ይበቃል፡፡ አገር እያላቸው መንግሰት አለሁላችሁ እያላቸው በአገራቸው እንዳሉና መንግስት እንዳላቸው እንዲሰማቸው ያላደረጓቸው ነገሮች ጥንካሬያቸውን እያጎለበቱ ወደ ጥቃት ጫፍ ሲያደርሷቸው ስደትን መረጡ፡፡ አሁን የሚገኙበት አገር አገራቸው፤ ህዝቡም ህዝባቸው መንግስቱም መንግስታቸው እንዳልሆነ ቢያውቁም ከአገር እንዲወጡ ያደረጋቸው ጥቃት ስላልተከተላቸው ቢያንስ የአካል ደህንነት ይሰማቸዋልና የስደት አገራቸውን እንደ አገር መቁጠራቸው ግፋ ሲልም እንደ ስድስተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ፓትርያርክ ዜግነት መቀየራቸው የሚጠበቅ ይሆናል ፡፡ በኢትዮጵያችን “አገሬ የት ነው” የሚል ጥያቄ ለማንሳት የሚያበቁ ጥቃቶች በየዕለቱ የሚፈጸሙ መሆናቸውን ዜግነቱ ድንግርግር ላለው የአገሬ ልጅ መንገር ትርፉ ማሰልቸት ነው፡፡

ከሰሞኑ ግለሰባዊና ድርጅታዊ የነበረው ጥቃት መልኩን ቀይሮ ማህበረሰባዊ ገጽታ መላበሱን እየተመለከትን ነው፡፡ በቤኒሻንጉል ለአመታት ቤት ንብረት አፍርተው ሰላማዊ ኑሮ መስርተው የነበሩ ዜጎች “ክልላችሁ ባለመሆኑ አካባቢውን ልቀቁ” ተብለው ለስደት ተዳርገዋል፡፡ የእነዚህ ዜጎችን መፈናቀል በሰማንበት ወቅት በሳዑዲ አረቢያ የነበሩ ኢትዮጵያዊያን “ወደ አገራችሁ ተመለሱ” ተብለው ስለመፈናቀላቸው እያደመጥን ነበር፡፡ መቼም የሳዑዲው ይሁን ከገዛ አገር መፈናቀልን በምን ልንገልጸው እንችላለን፡፡ እርግጥ ነው በአንድ ክልል ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ለግጭት የመዳረጋቸው ዜና አዲስ አይደለም፡፡ ከመሬትና የተፈጥሮን ጸጋ ከመጠቀም አንጻር ግጭቶች መፈናቀሎች ይፈጠራሉ፡፡ ከግጦሽ መሬት ጋር በተያያዘ በተነሱ ግጭቶች የብዙዎች ህይወት ተቀጥፏል፡፡ እንዲህ አይነት ግጭቶች በተከሰቱ ቁጥር የፌደራል መንግስቱ ጣልቃ በመግባት ችግሩን ከስሩ ለመቅረፍ ከመሞከር ይልቅ ወታደሮቹን እያዘመተ ግጭቱ ካጠፋው የሰው ህይወት በላይ እንዲጠፋ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

ገዢው ግምባር ኢህአዴግ ይህችን አገር በብረት መግዛት ከጀመረበት ግዜ አንስቶ በተለያዩ ቦታዎች መፈናቀሎች ተከስተዋል፡፡ እነዚህ መፈናቀሎች አደረሱ ከምንላቸው የመብት ረገጣዎች፣ የሞራል ድቀቶች ባልተናነሰ ህይወት ተገብሮባቸዋል፡፡ በበደኖና በአርባጉጉ የደረሱ ሰቆቃዎች የጥቃቱን አድራሾች ማንነት ያልለዩ ከመሆናቸውም በላይ የድርጊቱ ፈጻሚዎች በፍትህ አደባባይ ቀርበው የእጃቸውን አለማግኘታቸው የጉራፈርዳው ትራጄዲ እንዲፈጸም ምክንያት ሆኗል፡፡ ጉራፈርዳ ወረዳ የነበሩ ዜጎችን እንዲፈናቀሉ ያደረጉ ሆዳሞች የተፈናቃዮቹን መሬት የግላቸው ማድረግ የመቻላቸው ዜናም በየክልሉ የሚገኙ ሆዳሞችን ማነቃቃቱ የሚጠበቅ ነው፡፡

በዚህ መነሻነትም ይመስለኛል በቤኒሻንጉል የአማሮች መሰደድ የተከሰተው፡፡ የኢትዮጵያ የወቅቱ ህገ መንግስት ዜጎች በፈለጉበት አካባቢ የመኖር፣የመስራትና ሀብት የማፍራት መብት እንዳላቸው የሚደነግግ ቢሆንም ነባራዊው እውነታ ግን ከዚህ ጋር በእጅጉ የሚጣረስ ነው፡፡

የዜጎች መብት በጥቂት ነውረኞች ሲደፈጠጥ ለምን የሚል ስርዓት ባለመዘርጋቱም በደህናው ጊዜ አገሬ ነው በሚል ኢትዮጵያዊ ስሜት ተነሳስተው ከቀያቸው ርቀው ኑሮ የመሰረቱ ዜጎች ድንጋጤ ውስጥ እንዲገቡና የሰቀቀን ህይወት እንዲመሩ እየተደረጉ ነው፡፡ኢህአዴግ በስልጣን ላይ እስካለ ድረስም እንዲህ አይነት ዘግናኝ ዜናዎችም መደመጣቸው አይቀሬ ነው፡፡ ነገሩ ስር እየሰደደና በሁሉም ክልሎች የሚገኙ ሆዳሞች ምሳቸውን ለማግኘት የእባብ መርዛቸውን ከመርጨታቸው በፊት አገሪቱን በቀደመው የኢትዮጵያዊነት ጠበል የሚያጠምቅ መሲህ መፈጠር ይኖርበታል፡፡ እርግጥ ነው ይህ መሲህ ከድንግሊቱ የሚወለድ ባለመሆኑ ‹‹ድንግሏን››መጠበቅ አይኖርብንም፡፡ወይም መቼ ይሆን መሲህው የሚወለደው በማለት ለጠቢባን ስንቅ መሰነቅ አይጠበቅብንም፡፡ምክንያቱም አዳኙ



የሚመጣው እኛ ለዚህች አገር ከሚኖረን ርዕይ ነው፡፡አገሬ ይህችው ኢትዮጵያ እንጂ ሌላ አይደለችም የምንል ከሆነ ምድራችን በጥቂት ሆድ አደር በቀቀኖች የሁቱና ቱትሲ አይነት እልቂት ሳይከሰትባት፣እርስ በእርሱ የማይተማመንና ብሄራዊ ስሜት የሌለው ማህበረሰብ ሳይፈጠርባት የበኩላችንን ለማድረግ እንነሳ፡፡ የቤኒሻንጉል ህዝብ አማርኛ ተናጋሪ የሆኑ ወንድሞቹን ከክልሉ እንዲሰደዱ አደረገ ማለት ለእኔ ህዝቡን መስደብ ነው፡፡የኢትዮጵያ ህዝብ ላለፉት 22 ዓመታት እንዲጋት የተደረገው የዘውጌ ፖለቲካ አንድነቱን ሳይንድበት እስካሁን ኢትዮጵያዊነት በሚሰኝ አንድ ጥላ በመሰብሰብ አገሪቱን ማባሪያ ወደሌለው ዕልቂት ሊከታት ይችል የነበረን ሃላፊነት የጎደለው ፖለቲካ ታግሏል፡፡ ነገር ግን ይህ መስመር ዋጋ አላስከፈለንም ማለት አይቻልም፡፡ውድ የኢትዮጵያ ልጆች መተኪያ የሌለውን ህይወታቸውን ገብረውበታል፡፡ለአመታት የደከሙበትን ንብረት ሆዳሞች ተቀራምተውታል፡፡

የክልል ወይም የፌደራሉ መንግስት ለም መሬትን ለውጪ አገራት ኢንቨስተሮች ያለ ገደብ በመስጠት ዜጋውን የበይ ተመልካች ማድረጋቸውም እየሰማነው ለምንገኘው ማፈናቀል የመሰረት ደንጊያ ሆኗል፡፡ዜጋውን ተጠቃሚ ያደረገ ፖሊሲ የሌለው ድኩም መንግስት ደግሞ የመጀመሪያ ትኩረቱ ወደ አገር እንዲገቡ ያደረጋቸው የውጪ ኢንቨስተሮች እንጂ ዜጋው ባለመሆኑ ጉዳዩ የክልሉን መንግስት የሚመለከት በመሆኑ ጣልቃ አልገባም ማለቱ የሚጠበቅ ነው፡፡ከጥቂት ጊዜ በፊት በ ኡጋዴን በቻይና ሰራተኞች ላይ የደረሰውን ጥቃት አቀነባበሩ ያላቸውን ሀይሎች መንግስት በቁጥጥር ስር ለማዋል ምን ያህል ፈጣን እንቅስቃሴ ማድረጉን የሚያስታውሱ ሰዎች ቻይናዊነትንና ኢትዮጵያዊነትን ጠረጴዛው ላይ በማቅረብ ለዚህ መንግስት የትኛው እንደሚቀርብ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ የክልል መንግስታት ተወላጆች ከሚሏቸው ዜጎች የሚነሳባቸውን የመልካም አስተዳደር፣የኢኮኖሚና ፖለቲካዊ ጥያቄዎች እንዲህ አይነት ሆድ አደር ካድሬዎችን በማሰማራት ማድበስበስ እንደሚችሉ ገምተው ከሆነ ተሳስተዋል፡፡እርግጥ ነው ዜጎችን በማፈናቀል ጥቂት መሬት ተገኝቶ ይሆናል፡፡የዚህ ጦስ ግን ዘመን ተሻጋሪ ነው፡፡ ሆዳሞች ኢትዮጵያዊንትን አሸንፈው እነመለስ በ1997 ምርጫ ወቅት እንደፎከሩብን ኢንተርሀሙዌ እንደማይወለድ አምናለሁ፡፡የአማራው መፈናቀል የጉራጌው፣የትግሬው፣የኦሮሞውናየሌላውም መፈናቀል እንጂ ኦሮሞው፣ቤኒሻንጉሉ ወይም ሀድያው አፈናቃይ አይደለም፡፡የኢትዮጵያ ህዝብ ወይም አማራው የበደኖው፣የቤኒሻንጉሉና የጉራፈርዳው አፈናቃዮችን ማንነት አብጠርጥሮ የሚገነዘብ በመሆኑ ጊዜው ሲደርስ ማንን በፍርድ አደባባይ እንደሚያቆም ያውቃል፡፡አማራው በኦሮሞው ፣ጉራጌው በትግሬው እንዲነሳ የሚፈልጉና አጀንዳ በማስለወጥ የስልጣን ጊዜያቸውን ማርዘም የሚመኙ ሆዳሞች ከርሳቸውን ሳይሞሉ የክፉ ህላማቸው ሳይሰምር እጅ ከፍንጅ መያዛቸው አይቀሬ መሆኑ በተስፋ እንድታሰር ያደርገኛል፡፡ይህ የክፉት ቀን እንዲያጥር ግን አገሬን ባዮች ከማጀት መብሰልሰል ወደ አደባባይ መውጣት ግድ ይላቸዋል፡፡ እናም የቤኒሻንጉሉ ግፍ የሚያስተጋባው የጥሪ ደወል‹‹አገሬን የምትል በየት ነህ ››የሚል ነው፡፡ይህን የሚሰማም እነሆ በዚህ ነኝ ይበል፡፡

# በቤንች ማጂ አማርኛ ተናጋሪዎችን ማፈናቀል ዳግም ተጀመረ

በደቡብ ክልል ቤንች ማጂ ዞን በሚገኘው ሜኒት ወልድያ ወረዳ በተለይም ዘንባብና አርፋጅ ቀበሌ ነዋሪዎች በካከል ከ350 በላይ የአማርኛ ተናጋሪ ዜጎች ተፈናቅለው በወረዳው አካባቢ በሚገኝ ጫካ ውስጥ ተጠልለው እንደሚገኙ አስታውቀዋል።

ማን እንዳደራጃቸው በማይታወቁ ግለሰቦች ከመኖሪያ አካባቢያቸው 61 ከብቶችና ግምቱ ያልታወቀ እህል ተዘርፈው አካባቢያቸውን ጥለው ለመውጣት የተገደዱት አማርኛ ተናጋሪ ተፈናቃዮቹ ተሸሽገው ባሉበት ጫካ ለከፍተኛ ርሃብና ውሃ ጥም መዳረጋቸውን ለፍኖተ ነፃነት ጨምረው ገልፀዋል።

ከተፈናቃዮች መካከልም 4 በግፍ መገደላቸውንና የወረዳው አስተዳደር አካላት "እናጣራለን" ከማለት ውጭ ምንም መልስ ባለመስጠታቸው ጉዳዩ እየባሰ በመሄዱ ንብረቶቻቸው ተዘርፈው በአሁን ወቅት ለዓመታት የኖሩበትን አካባቢ ጥለው በጫካ መጠለልን መምረጣቸውን ተፈናቃዮቹ በተለይ ለፍኖተ ነፃነት ገልፀዋል።

እንደተፈናቃዮቹ ገለፃ ከሆነ በአሁን ወቅት ከወረዳው ፖሊሶች ውጭ የአስተዳደሩ አካላት በግፍ መፈናቀላችንን በተመለከተ ያላቸውን ውሳኔ እንዲያሣውቁን ብንጠይቅም ምላሽ የሰጠን ባለመኖሩ አሁንም ለከፍተኛ ችግር በመጋለጣችን የሚመለከተው የመንግስት አካል ምላሽ እንዲሰጠን እንፈልጋለን ብለዋል።

በተለይ ጉዳዩ ላይ የደቡብ ክልላዊ መንግስት የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ኃላፊ የሆኑት አቶ ሁሴን በበኩላቸው "በአሁን ወቅት በክልሉ ምንም ዓይነት የአማርኛ ተናጋሪ ዜጎችን ማፈናቀል ስራ አልተካሄደም፤ የተላለፈ መመሪያም የለም፤ እንደውም በተለያየ ምክንያት ከተለያየ ቦታ ወደ ክልሉ የመጡትን እንኳ እየተንከባከብን ነው" ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል።

ከተፈናቃዮቹ ጋር በተያያዘ የአማራ ክልላዊ መንግስት ያለውን አቋም ለማረጋገጥ የክልሉ ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ኃላፊ ወደ ሆኑት አቶ ንጉሴ ጋር ደውለን ጉዳዩን ስናነሳላቸው ስልካቸውን የጋዜጠኛው ጆሮ ላይ በመዝጋታቸው የክልሉን መንግስት አቋም ልናረጋግጥ አልቻልንም። በተለያየ የሀገሪቱ ክፍል ዜጎችን የማፈናቀሉ ጉዳይ እየቀጠለ በመሆኑና ዜጎች በሀገራቸው የመኖር ነፃነታቸውን የማክበርና የማስከበር ኃላፊነት ምን ያህል እየተተገበረ ነው የሚለውንና የዜጎችን ከነበሩበት ቦታ ቋንቋን መሰረት በማድረግ ብቻ ማፈናቀል መንግስት የሚከተለው ፖሊሲ ትግበራ መሆኑን ለማረጋገጥ የፌደራሉ የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት ምክትል ሚኒስትር አቶ ሽመልስ ከማልን ጠይቀናቸው "አሁን ከሰው ጋር ነኝ ትንሽ ቆይተህ ደውል(ሰዓት ቀጥረው) ቢሉም ባሉት ሰዓት ሲደወልላቸው ስልካቸውን ሊያነሱ አልቻሉም።

ከዚህ በፊት በዚሁ ቤንች ማጂ ዞን ጉራፈርዳ ወረዳ የሚኖሩ አማርኛ ተናጋሪዎች በክልሉ መንግስት ፕሬዘዳንት አቶ ሽፈራው ሽጉጤ ልዩ ትዕዛዝ ፤ በቅርቡ ደግሞ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ያሶ ወረዳ ያሉ አማርኛ ተናጋሪ ዜጎች ያፈሩትን ሀብትና ንብረታቸውን ጥለው እንዲፈናቀሉ መደረጉ ይታወቃል።

# የታፈኑት የአንድነት አመራር የታሰሩበትን ምክንያት የሚገልፅ ማስረጃ ተከለከሉ

በሰሜን ጎንደር በምዕራብ አርማጨሆ ወረዳ የአንድነት ፓርቲ አመራር የሆኑት አቶ አንጋው ተገኝ ከመጋቢት 13 ቀን 2005ዓ.ም. ጀምሮ በዞኑ የደህንነት ኃይሎች ታፍነው ከታሰሩ በኋላ ሲለቀቁ ማስረጃ እንደተከለከሉ ተገለፀ።

የደህንነት ኃይሎቹ አቶ አንጋው ተገኝን አፍነው ወዳልታወቀበት ቦታ ከወሰዷቸው በኋላ ታችኛው አርማጭሆ ፖሊስ ጣቢያ በመውሰድ እጅ እግራቸውን በካቴና አስረው ለ6 ቀናት ካቆዩአቸው በኋላ መልቀቃቸው ታውቋል።

አቶ አንጋው የታሰሩበት ምክንያትን በተመለከተ ወጣቶችን እያሰለጠንክ ወደ ኤርትራ ትልካለህ በሚል እንደነበረና በመጨረሻም ከእስር ከለቀቋቸው በኋላ ምዕራብ አርማጨሆ ወደ ስራ ገበታቸው ሲሄዱ መስሪያ ቤታቸው የቆዩበትን ምክንያት በፅሑፍ ማስረጃ ካላቀረቡ ደመወዝ እንደማይከፍላቸው የወረዳው ኃላፊ አቶ ገ/መድህን አረጋግጠዋል።

በዚህም ምክንያት አቶ አንጋው ተገኝ በእስር ላይ መሆናቸውን ከነምክንያቱ የሚገልፅ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ለመርማሪው ፖሊስ ኢንስፔክተር ቸርነት ጥያቄ ቢያቀርቡም ፈቃደኛ እንዳልሆኑላቸው ገልፀውልናል። መርማሪው ፖሊስ ኢንስፔክተር ምህረቱ በበኩላቸው "እኛ ማስረጃውን አልከለከልንም፣ ከሚሰሩበት መስሪያ ቤት ጥያቄ በደብዳቤ ሲያቀርቡልን እንፅፋለን ብለን ከአቶ አንጋው ጋር ተነጋግረናል" ሲሉ በተለይ ለፍኖተ ነፃነት ገልፀዋል። አቶ ገ/መድህን ደግሞ "ያሰራቸው አካል ያሰረበትን ቀንና ምክንያት ይግለፅልን እንጂ እኛ በደብዳቤ ልንጠይቅ አንችልም" ሲሉ ምላሽ ሰጥተውናል።

# ምርጫ እስኪያልፍሙዚቃ ቤቶች የቴዲ አፍሮና የፀጋዬ እሸቱን ዘፈኖች መክፈት ተከለከሉ

በአዲስ አበባ የተለያዩ ስፍራዎች በሚገኙ መዝናኛዎችና ሙዚቃ ቤቶች በሚያዝያ መጀመሪያ የሚደረገው የአካባቢ ምርጫ ሳያልፍ ሀገር ፍቅር ስሜት የሚቀሰቅሱ ዘፈኖችን እንዳይከፍቱ ክልከላ ተደረገ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ በሚደረገው የከተማ መስተዳድርና የአካባቢ ምርጫ ብቻውን የሚወዳደረው ኢህአዴግ በካድሬዎቹ አስገራሚ ትዕዛዞችን እየሰጠ እንደሚገኝ የፍኖተ ነፃነት ምንጮች ጠቆሙ።

በአዲሱ ትዕዛዝ መሰረት ምርጫው እስኪያልቅ ድረስ ሙዚቃ ከፍ አድርገው የሚያጫውቱ ሙዚቃ ቤቶችና የመዝናኛ ስፍራዎች የሀገር ፍቅር ስሜት የሚቀሰቅሱና ስለባንዲራ የተዜሙ ዘፈኖችን መክፈት ተከልክለዋል። በትዕዛዙ በተለይ የተከለከሉት የቴዲ አፍሮና የፀጋዬ እሸቱ አዲሱ አልበም ላይ የተካተቱት ዜማዎች ይጠቀሳሉ።

ነጋዴዎቹ "ክልከላው ከምርጫው ጋር ምን እንዳያያዘው አልገባንም፣ሆኖም ከመንግስት የመጣ ትዕዛዝ ስለሆነ ላለፉት ሁለት ሳምንታት ዘፈኖቹን ማጫወት አቁመናል" ብለዋል። ነጋዴዎቹ ጨምረው ለፍኖተ ነፃነት እንደገለፁት በተለያየ ጊዜ ለቁጥጥር የሚመጡት የወረዳ ካድሬዎች የተከለከሉትን ዘፈኖች ተከፍቶ ከሰሙ ዛቻና ማስፈራሪያ እንደሚያደርሱባቸው ። "የቴዲን ዘፈን በተለያዩ ወቅቶች አትክፈቱ ተብለን እናውቃለን" የሚሉት ነጋዴዎቹ የፀጋዬ እሸቱ አዲሱ አልበም ውስጥ ያሉት ሀገርንና ባንዲራን የሚመለከቱ ዘፈኖች በሬዲዮ እየተለቀቁ እነሱ እንዳይከፍቱ መደረጋቸው እንዳስገረማቸው ገለፀዋል።

ምንጮቻችን ተዘዋውረው ያነጋገሯቸው ነጋዴዎች እንደገለፁት ይህ ክልከላ ጎልቶ የታየው በመርካቶና በፒያሳ አካባቢ ነው።

# አዲሱ የኤች አይ ቪ መድኃኒት ታካሚዎችን ለአሰቃቂ ሞት እየዳረገ ነው

በኢትዮጵያ የኤች አይ ቪ ኤድስ ሰለባ ሆነው የመድኃኒት ተጠቃሚ የሆኑ ታካሚዎች መንግስት ከቻይና አስመጥቶ እያከፋፈለ ያለው መድኃኒት ከፍቱንነቱ ይልቅ በአሰቃቂ ሁኔታ አቁስሎ እየገደለ መሆኑን ምንጮቻችን በተለይ ለፍኖተ ነፃነት ገለፁ፡፡

እንደምንጮቻችን ጥቆማ ከሆነ ቀደም ሲል መድኃኒቱ ይመጣ የነበረው በተባበሩት መንግስታት የዓለም የጤና ድርጅት በሚደረግ ዕርዳታ እንደሆነ እና ደረጃውን የጠበቀ መድኃኒትም ከደቡብ አፍሪካ ይገባ እንደነበረ ተጠቁሟል፡፡ በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣናት ለሙስና እንዲመቻቸው ደረጃውን ያልጠበቀ መድኃኒት በርካሽ ዋጋ ከቻይና በማስመጣት ተጠቃሚዎች ላይ ከፍተኛ የጤና ችግር መፈጠሩን ጨምረው ገልፀዋል፡፡

አዲሱን ከቻይና የመጣውን የኤች አይ ቪ ኤድስ መድኃኒት የሚጠቀሙ ሰዎችም ሰውነታቸው ድንገት በመቆሳሰሉ ለአልጋ ቁራኛነት በመዳረግ ህይወታቸው እያለፈ በመሆኑ ጉዳዩን ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ቢያመለክቱም እስካሁን ምላሽ ባለመገኘቱ ለአደጋ እንደዳረጋቸው ስማቸውን መግለፅ ያልፈለጉ ምንጮች ለፍኖተ ነፃነት ገልፀዋል፡፡

በጉዳዩ ዙሪያ ምላሽ እንዲሰጡን የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ የሆኑትን አቶ አህመድ ኢማኖን ሐሳብ ለማካተት ተደጋጋሚ ጥረት ብናደርግም ስልካቸውን ሊያነሱልን አልቻሉም፡፡

ሌላው ጉዳዩ ይመለከተዋል የተባለው የኢትዮጵያ መድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን የምግብና መድኃኒት ፈቃድ ዳይሮክተሬት ዳይሬክተር ተወካይ የሆኑት አቶ ብኒያም ቢተው የኤች.አይ.ቪ ኤድስ መድኃኒት ለኢትዮጵያውያን ተጠቃሚዎች ይመጣ የነበረው ከደቡብ አፍሪካ መሆኑንና አሁን ግን ከቻይና መምጣቱን አምነው የተቀየረበትና እያስከተለ ስላለው ጉዳት ሲጠየቁ ግን "የማውቀው ነገር የለም፤ እንደውም በህዝብ ግንኙነት በኩል ካልመጣችሁ የምሰጣችሁ መረጃ የለኝም ፤ እኔ ተወካይ እንጂ ኃላፊ አይደለሁም" ሲሉ ለፍኖተ ነፃነት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ የጉዳዩን አሳሳቢነት በመረዳት ወደ ህዝብ ግንኙነት ኃለፊ ብናመራም በቦታው ላይ ያሉት አቶ አበራ ደነቀ የሚባሉ ተወካይ በመሆናቸው መረጃው እንደሌላቸውና በይበልጥ በቀጥታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተወያይተው ወደፊት መልስ ሊሰጡ እንደሚችሉ ከመጠቆም ውጭ ለማረጋገጥም ሆነ ለማስተባበል አልደፈሩም፡፡ ይሁን እንጂ የመድኃኒቱ ለውጥ የገባቸው ተጠቃሚዎች በስጋት ላይ መሆናቸውን በመናገር ላይ ናቸው፡፡

# ‹‹የሃይማኖት ነጻነት በኢትዮጵያ አልተከበረም››

## ጠበቃ ተማም አባቡልጉ

የሃይማኖት ነጻነትና ህገ መንግስት በሚል ርዕስ በአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ አዳራሽ እሁድ መጋቢት 29 ቀን 2005 ዓ.ም በተዘጋጀው የፓናል ውይይት የጥናት ጽሁፍ ያቀረቡት ታዋቂው የህግ ባለሙያ አቶ ተማም አባቡልጉ በኢትዮጵያ የሃይማኖት ነጻነት ተከብሯል ለማለት እንደሚቸገሩ ገልጸዋል፡፡

የሎሬት ጸጋዬ ገ/መድህንን ‹‹ሰቆቃወ ጴጥሮስ›› የሚለውን የግጥም ስራ በማንበብ ጥናታቸውን ያቀረቡት ጠበቃ ተማም በህገ መንግስቱ ሃይማኖታዊ መንግስት እንደማይኖርና መንግስትና ሃይማኖት እንደተለያዩ መጠቀሱን በመያዝ ብቻ የሃይማኖት ነጻነት ተከብሯል ማለት አዳጋች መሆኑን በማስመር የሃይማኖት ነጻነት ተከብሯል ማለት የሚቻለው ‹‹የሃይማኖት ነጻነት ጥሰት ሲደርስበት በአድራሾቹ ላይ ሊጣል የሚገባው የወንጀልና የፍትሐ ብሄር ቅጣት በማያሻማ መልኩ በህግ ተደንግጎ ቢሆን ነበር›› ብለዋል፡፡ በትምህርት ቤቶችና በአንዳንድ መስሪያ ቤቶች በተለይም ሙስሊም ኢትዮጵያዊያንን እምነታቸው የሚጠይቃቸውን የአምልኮ ስርዓት እንዳይፈጽሙ የሚያደርጉ ደንቦች እየጸደቁ መሆናቸውን እምነትን ከመግለጽ ነጻነት አንጻር አጥብቀው የተቃወሙት ጠበቃው‹‹ሙስሊሙ በቀን አምስት ግዜ እንዲሰግድ የእምነቱ መመሪያው ያዘዋል፡፡ በአንጻሩ ደንቦቹ ሲወጡ ይህንን ግምት ውስጥ አለመክተታቸው ችግሮች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኗል›› ብለዋል፡፡

መንግስት በሽብርተኝነት ከስሶ ወህኒ ባወረዳቸው የሙስሊሙ መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴዎች ላይ እየደረሰ ያለው የመብት ረገጣ መንግስት እንደሚለው ሳይሆን ከሃይማኖት ነጻነት ጋር የተያያዘ ጥያቄ በማንሳታቸው መሆኑን የገለጹት አቶ ተማም ‹‹ጥብቅና የቆምኩላቸው ደምበኞቼ እንደነገሩኝ ከሆነ መንግስት ከሊባኖስ የአህባሽን መምህራን በማምጣት ይህንን የእስልምና አስተምህሮ በሃይል ለመጫን ሞክሯል፡፡ እነርሱ የተቃወሙት መንግስት እዚህ ውስጥ በመግባት ይህንን ተከተሉ ማለት አይገባውም ማለት ነው፡፡›› ብለዋል፡፡

በፓናል ውይይቱ ላይ የተካፈሉ ተሰብሳቢዎች ለጠበቃው የተለያዩ ከውይይቱ ማዕቀፍ ያልወጡ ጥያቄዎችን ያቀረቡ ሲሆን አቶ ተማም ምላሻቸውን በመስጠት የውይይቱ ፍጻሜ ሆኗል፡፡

# አንድነት ፓርቲ ማተሚያ ማሽን በመግዛት የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣን ህትመት ለማስቀጠል የገቢ ማሰባሰቢያ መርሀግብር ጀምሯል

እርስዎም ፡-

. ኩፖን በመግዛት

. የቃልኪዳን ሰነድ በመሙላት

. አቢሲኒያ ባንክ ጠመንጃ ያዥ ቅርንጫፍ የባንክ ሒሳብ ቁጥር 47 ገቢ በማድረግ አጋርነትዎን ያረጋግጡ

ለተጨማሪ መረጃ

0933-89-17-66 እና
0933-89-17-67 ይደውሉ
udjparty@gmail.com

ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ወደ ህትመት እንድትመለስ በመርዳት መረጃ የማግኘት መብትዎን ያስከብሩ!!

ፍኖተ ነፃነት

የኢትዮጵያን ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ